03

3ኛ ዓመት ቁጥር 25
3rd year N0 25

ባህር ዳር መጋቢት 1 ቀን1990
Bahir Dar,10th March 1998

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ
የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ምክር ቤት

ዝክረ ሕግ
ZIKRE HIG

OF THE COUNCIL OF THE AMHARA NATIONAL REGIONAL STATE
IN THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

የአንዱ ዋጋ ብር 1.00	በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ምክር ቤት ተጠባባቂነት የወጣ	የፖ. ሣ. ቁ P. O. Box 312

ግ ው ጪ	CONTENTS
አዋጅ ቁጥር 25/1990 የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የገበሬዎች ጎብረት ሥራ ማህበራት ማስፋፊያ ጽ/ቤትን ለማቋቋም የወጣ አዋጅ	Proclamation N° 25/1998 A proclamation to Provide For The Establishment of Agricultural Cooperatives Promotion Office Of The Amhara National Regional State
ገፅ 6	Page 6

አዋጅ ቁጥር 25/1990
የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የገበሬዎች የጎብረት ሥራ ማህበራት ማስፋፊያ ጽ/ቤትን ለማቋቋም የወጣ አዋጅ

በአማራ ብሔራዊ ክልል የሚገኙ ገበሬዎች ገንዘባቸውን ፣ጉልበታቸውንና ዕውቀታቸውን በማቀናጀት በራሳቸው ፍላጎት በማኅበር ተደራጅተው ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ችግሮቻቸውን እንዲፈቱ ማድረግ አስፈላጊ ስለሆነ፤

ገበሬዎች በማህበራቸው አማካኝነት የግብርና ምርትን ለማሳደግ የሚያስችሉ ዘመናዊ የግብርና ቴክኖሎጂዎችን ፣የኢንዱስትሪ ውጤቶችንና ፣ የብድር

PROCLAMATION N° 25/1998
A PROCLAMATION TO PROVIDE FOR THE ESTABLISHMENT OF AGRICULTURAL COOPERATIVES PROMOTION OFFICE OF THE AMHARA NATIONAL REGIONAL STATE

Where as, it has become necessary to enable the farmers in the region to solve economic and social problems by being organized in cooperatives based on their interest by coordinating their money, knowledge and potential.

Where as it has become essential to create conducive atmosphere for the farmers so that through their cooperatives be able to adequately

190

190

አገልግሎት እንዲያገኙና በነፃ ገበያ ተወዳድረው ምርታቸውን በተሻለ ዋጋ ለመሸጥ የሚያስችላቸውን ዑኔታ ማመቻቸት አስፈላጊ በመሆኑ ፤

በሽግግር መንግስት በወጣው የገበሬዎች የኅብረት ሥራ ማህበራት አዋጅ ቁጥር 85/1986 መሠረት ለተቋቋሙና ወደፊትም በዚህ አዋጅ መሠረት ለሚቋቋሙ ማህበራት ድጋፍ የሚሠጥ፣ የኅብረት ሥራ ማህበራትን የሚያስፋፋና የሚያስተባብር አንድ የመንግስት አካል ማቋቋም አስፈላጊ በመሆኑ ፤

የአማራ ብሄራዊ ክልል መንግስት ም/ቤት በክልሉ ህገ - መንግስት አንቀጽ 49/3/1 መሠረት የሚከተለውን አውጇል።

ክ ፍ ል አ ን ድ
ጠ ቅ ላ ላ

1. አ ጭ ር ር ዕ ስ

ይህ አዋጅ ''የአማራ ብሄራዊ ክልል የገበሬዎች ኅብረት ሥራ ማህበራት ማስፋፊያ ጽ/ቤት ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 25/1990 ''ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

2. ት ር ጓ ሜ

የቃሉ አግባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ:=

1. ''የህብረት ሥራ ማኅበር'' ማለት የገበሬዎች የኅበረት ሥራ ማህበር ማለት ነው።
2. ''ክልል '' ማለት የአማራ ብሄራዊ ክልል ማለት ነው።
3. ''መንግስት''ማለት የአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት ማለት ነው።
4. ''ጽ/ቤት'' ማለት በዚህ አዋጅ መሠረት የተቋቋመ የገበሬዎች ኅብረት ሥራ ማህበራት ማስፋፊያ ጽ/ቤት ነው።

ክ ፍ ል ሁ ለ ት

ስለ ገበሬዎች ኅብረት ሥራ ማህበራት ማስፋፊያ ጽ/ቤት መቋቋም ፣ ተጠሪነት፣ የጽ/ቤት አደረጃጀትና ዓላማዎች፣

3. ስለ ጽ/ቤቱ መቋቋምና ተጠሪነት

1 .የአማራ ብሄራዊ ክልል የገበሬዎች የኅብረት

supply modern agricultural technologies, industrial products and credit services which will enable them to grow their agricultural production and compete in the market economy to sell their production with a better price.

Where as, it has been found essential to establish a government organ which can support, promote and coordinate agricultural cooperatives which have been established pursuant to agricultural cooperatives establishment proclamation No 85/1994 that has been proclaimed by transitional government and cooperatives to be establish according to this proclamation.

Now therefore, the council of the Amhara National Regional State pursuant to subarticle 3/1 of Article 49 of the constitution of the region, here by proclaimed as follows.

PART ONE
GENERAL

1. **Short tittle**

This proclamation may be cited as ''The Amhara National Regional Agricultural cooperatives promotion office establishment proclamation No 25 /1998''

2. **Definition**

In this proclamation, unless the context otherwise requires.

1.''coopratives'' means the agricultural cooperatives.
2.''Region'' means the Amhara National Region

3.''State'' means the Amhara National Regional State
4.''office'' means Agricultural cooperatives promotion office established pursuant to this proclamation.

PART TWO
Establishment, Accountability, Organization and Objectives of the Agricultural Cooperatives Office

3 .Establishment and Accountability

1.The Amahara National Region

ሥራ ማኅበራት ማስፋፊያ ጽ/ቤት /ከዚህ በኋላ የገበሬዎች የኅብረት ሥራ ማህበራት ማስፋፊያ ጽ/ቤት/ እየተባለ የሚጠራ ራሱን የቻለ እና ህጋዊ ሰውነት ያለው የመንግስት መ/ቤት ሆኖ በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል።

2. ይህ ጽ/ቤት ተጠሪነቱ ለአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴና ለክልሉ ርዕሰ መስተዳድር ይሆናል።

4. የጽ/ቤቱ አደረጃጀት

1. የገበሬዎች የኅብረት ሥራ ማህበራት ማስፋፊያ ጽ/ቤት በክልሉ የሚኖም የጽ/ቤት ኃላፊና ለሥራው የሚያስፈልጉ ሌሎች ሠራተኞች ይኖሩታል።
2. የጽ/ቤቱ ዋና መ/ቤት ባህር ዳር ከተማ ይሆናል።
3. ጽ/ቤቱ በዞንና በወረዳዎች የሚቋቋሙ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ይኖሩታል።

5. የጽ/ቤቱ ዓ ላ ማ ዎ ች

ጽ/ቤቱ የሚከተሉት ዓላማዎች ይኖሩታል፣

1. በክልሉ ውስጥ ለሚኖሩ ገበሬዎች ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጠቀሜታ ሊያስገኙ የሚችሉና በአባላቱ ፍላጎት ላይ የተመሠረቱ የተለያዩ ዓይነት የኅብረት ሥራ ማህበራትን እንዲደራጁ ምቹ ሁኔታዎችን መፍጠር፣
2. የግብርና ምርት ውጤቶችን ለማሳደግ የሚያስችሉ ግብዓቶችንና ለኑሮ የሚያስፈልጉ ሸቀጣ ሸቀጦችን ማህበራት እንዲያገኙ እገዛ ማድረግ ፣
3. የህብረት ሥራ ማህበራት የግብርና ምርት ውጤቶችን ከገበሬው በመግዛትና ለገበያ በማቅረብ የአባላቶቻቸውን ጥቅም ለማስጠበቅ በሚያደርጉት ጥረት ተገቢውን ድጋፍ የመስጠትና
4. ማህበራት በነፃ ገበያ ኢኮኖሚ ውስጥ ተወዳዳሪ ሆነው በክልሉ ልማት ውስጥ ጉልህ ተሳትፎ እንዲኖራቸው ማድረግ።

ክ ፍ ል ሶ ስ ት
የገበሬዎች የኅብረት ሥራ ማህበራት ማስፋፊያ ጽ/ቤትና የኃላፊው ጠቅላላ ሥልጣንና ተግባር

6. የገበሬዎች የኅብረት ሥራ ማህበራት ማስፋፊያ ጽ/ቤት ሥልጣንና ተግባር

ጽ/ቤቱ የሚከተሉት ስልጣንና ተግባር ይኖሩታል ፤

1. የገበሬዎች የኅብረት ሥራ ማህበራትን በሚመለከት የፖሊሲ ሃሣቦች ያመነጫል ፤የጥናትና ምርምር ተግባራትን ያከናውናል ፤ ለኅብረት ሥራ ማህበራት እድገት የሚጠቅሙና በገበሬው ተሳትፎ የሚሠሩ የልማት ፕሮጀክቶችን ያዘጋጃል ፤

Agricultural cooperative promotion office,is here by established as an autonomous and legal organ of the regional state pursuant to this proclamation.

2.The office is accountable to the executive committee and the president of the Amhara National Regional State.

4 Organization

1.The office shall have the office head to be assigned by the region and other staff necessary to carry different responsibilities.
2. The head office shall be in Bahir Dar
3. The office establish branch offices in different zones and woredas.

5. Objectives

The office shall have the following objectives

1. To create conducive atmosphere for farmers living in the region to organize different kinds of Agricultural cooperatives based on their economic and social interests and benefits.
2. To support cooperatives to get modern technologies that are necessary for the improvement of their agricultural productions and other commodities needed for life
3. To support the cooperatives in their effort to keep the benefit of their members by buying agricultural products from the farmers and get to the market.
4. To enable cooperatives competent in the market economy and play their role in the economic development of the region.

PART THREE
POWER AND DUTIES OF THE AGRICULTURAL COOPERATIVES PROMOTION OFICE AND THE HEAD

6.Power and Duties of the Agricultural cooperatives promotion offic

The office shall have the following powers and duties.

1. Develop policy issues concerning cooperatives in the region, conduct study and research activities, prepare development projects essential for the improvement of cooperatives and which can be implemented through the participation of farmers and up on approval implement the same

192

የአፈፃፀም ስትራቴጂና ቅደም ተከተል ያወጣል ፤ሲፀድቅም በተግባር ያውላል።

2. የኅብረት ሥራ ኤክስቴንሽንን በገጠሩ ለማስፋፋትና ለማዳበር የሚያስችሉ ተከታታይ የትምህርትና የሥልጠና ፕሮግራሞችን በማዘጋጀት ለኅብረት ሥራ ማህበራት አባላት ፣ለሠራተኞችና ለኅብረት ሥራ ባለሙያዎች ይሠጣል ፣

3. በገበሬው ፍላጎት መሠረት ማኅበራት እንዲደራጁ አስፈላጊውን እገዛ ያደርጋል ፣

4. ገበሬዎች በኅብረት ሥራ ማህበራቸው በኩል የግብርና ምርት ማሣደጊያ ግብዓቶችን ፣የኢንዱስትሪ ውጤቶችን ፣በጥናት ላይ የተመሰረተ ብድር እንዲያገኙና የግብርና ምርታቸውን በተሻለ ዋጋ በመሸጥ ተጠቃሚ የሚሆኑበትን ሁኔታ ያመቻቻል፣

5. ማኅበራት አስፈላጊና ወቅታዊ የገበያ መረጃ እንዲያገኙ በማድረግ በነፃ ገበያ ተወዳዳሪ ሆነው ተጠቃሚ የሚሆኑበትንና ለክልሉ የኢኮኖሚ ዕድገት የአቅማቸውን ያህል የሚያበረክቱበትን ሁኔታ ያመቻቻል፣

6. አለም አቀፍ የኅብረት ሥራ መርሆዎችን መሠረት በማድረግ የክልሉን ተጨባጭ ሁኔታ በማገናዘብ በመንግስት ህግና መመሪያ ላይ ተመስርተው የተደራጁ ማህበራትን ይመዘግባል፣ የህጋዊ ሠውነት ማረጋገጫ ሠርቲፊኬት ይሰጣል ፣ይሠርዛል።

7. በክልሉ ውስጥ ከፍተኛ ደረጃ የኅብረት ሥራ ማህበራት እንዲቋቋሙ ሁኔታዎችን ያመቻቻል፣

8. የኅብረት ሥራ ማህበራት በሚዋሀዱበት ፣በሚለያዩበት፣ወይም በሚፈርሱበት ጊዜ በሽግግር መንግስት በወጣው አዋጅ ቁጥር 85/1986 እና በተከታታይ በሚወጡ የኅብረት ሥራ ማህበራት አዋጆች መሠረት እንዲፈፀም አስፈላጊ ክትትልና ድጋፍ ያደርጋል።

9. የኅብረት ሥራ ማህበራትን ገንዘብና ንብረት እንዳይባክን ወቅታዊ የሂሣብ ምርመራ በማካሄድ ያግዛል፣

10. የኅብረት ሥራ ማህበራትን የሚመለከቱ ህጎችን፣ ደንቦችን፣መመሪያዎችን በትክክል በሥራ ላይ መዋላቸውን ይከታተላል ፤ይቆጣጠራል፤

11. የጽ/ቤቱን ዕቅድና በጀት ያዘጋጃል፤ ሲፈቀድም በሥራ ላይ ያውላል ፤

12. የንብረት ባለቤት ይሆናል፣ውል ይዋዋላል ፣በስሙ ይከሣል፣ይከሰሳል ፤

13. ዓላማውን ለማስፈፀም የሚረዱ ሌሎች ተግባራትን ያከናውናል፤

2. prepare and render continuing education and training programs for members of cooperatives, personnel's and cooperative experts which enable to promote and consolidate cooperative extensions in the rural areas.

3. provide the necessary support to organize different types of cooperatives based on the interests of farmers.

4. Facilitate conditions by which farmers, through their cooperative, can get modern technologies that are necessary for the improvement of their agricultural productions, industrial products, study based credit and benefit by selling their productions with a better price.

5. Provide available timely market information to cooperatives, so that they will be able to compete in the market economy and play their role in the economic development of the region.

6. Register and issue certificate to cooperatives that are organized based on international cooperative principles and in line with the government laws and directives taking objective conditions of the region in to account.

7. Create conducive atmosphere for the establishment of high level cooperatives in the region.

8. Make the necessary follow up and support that cooperatives amalgamation, division and dessolution to be executed in line with the cooperatives establishment proclamation No 85/1994 of the transitional government and continuing cooperative proclamations.

9. Audit timely the accounts of cooperatives in order not to be misused .

10. Follow up and supervise laws, regulations and directives concerning cooperatives are executed approperatly.

11. Prepare plan and budget of the office and up on approval implement the same.

12. Own property, enter in to contract, sue and be sued, in its own name.

13. Perform such other activities necessary for the execution of its objectives.

7. **የገበሬዎች ጎብረት ሥራ ማህበራት ማስፋፊያ ጽ/ቤት ኃላፊ ሥልጣንና ተግባር**

የጽ/ቤቱ ኃላፊ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 6 ላይ ለጽ/ቤቱ የተሰጡትን ስልጣንና ተግባራት የሚያከናውን ሲሆን በተጨማሪም የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል።

1. የጽ/ቤቱን ሥራዎች ይመራል ፣ያስተዳድራል፣ይቆጣጠራል
2. የጽ/ቤቱን የአጭር፣ የመካከለኛና የረጅም ጊዜ እቅድ የሥራ ፕሮግራምና በጀት አዘጋጅቶ ያቀርባል፣ሲፈቀድም በሥራ ላይ ያውላል ፣
3. በመንግስት ሠራተኞች አስተዳደር ህግ መሠረት ሠራተኞችንይቀጥራል፣ያስተዳድራል፣ያሠናብታል።
4. ለጽ/ቤቱ በተፈቀደው በጀት ፣ሥራና ፅቅድ መሠረት የገንዘብ ክፍያ ይፈጽማል /
5. በህግ መሠረት በጽ/ቤቱ ስም የባንክ ሂሣብ ይከፍታል ፣ያንቀሳቅሳል፤
6. እንደአስፈላጊነቱ በዚህ አዋጅ የተሰጠውን ሥልጣንና ተግባር ለጽ/ቤቱ ሠራተኞች ውክልና ይሰጣል ፤
7. ጽ/ቤቱን በሚመለከት ረቂቅ ህጎችን ፤ መመሪያዎችን ለአማራ ብሄራዊ ክልል ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አቅርቦ ያስፀድቃል፤ሲፈቀድም በሥራ ላይ ያውላል፤
8. ስለ ሥራው አፈፃፀም በየጊዜው ለሚመለከተው አካል ሪፖርት ያቀርባል ፤
9. በክልሉ ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴና በርዕሰ መስተዳድሩ የሚሰጡትን ሌሎች ተመሳሳይ ሥራዎች ይፈጽማል።

ክ ፍ ል አ ራ ት
ል ዩ ል ዩ ድ ን ጋ ጌ ዎ ች

8. ስለ በጀትና የሂሳብ መዛግብት አያያዝ
   1. የጽ/ቤቱ የገንዘብ ምንጭ መንግስትና ሌሎች ይሆናሉ
   2. ጽ/ቤቱ የተሟላና ህጋዊ የሆነ የሂሳብ መዛግብት ይይዛል
   3. የጽ/ቤቱ የሂሣብ መዛግብትና ገንዘብ ነክ ሠነዶች በክልሉ ዋና አዲተር ወይም አቡ በሚሠይማቸው አዲተሮች በየዓመቱ ይመረመራሉ።
9. የ መ ሸ ጋ ገ ሪ ያ ድ ን ጋ ጌ
   1. ጽ/ቤቱ ከዚህ ቀደም የተቋቋሙ የጎብረት ሥራ ማህበራትን ሂሳብ በመመርመር እገዛ ያደርጋል።
   2. ጽ/ቤቱ በሚያደርገው የሂሳብ ምርመራ በማጎበራት ገንዘብና ንብረት ላይ ጥፋት

7. **POWERS AND DUITIES OF THE OFFICE HEAD**

The office head shall in addition to the powers and duties given to the office pursuant to article 6 of this proclamation, have the following power and duties.

1. Direct administer and supervise the activities of the office
2. prepare and submit short,midium and long term plan, annual action plan and budget of the office, and implement up on approval.
3. Employee, administer and dismiss the necessary employees in accordance with civil service regulations.
4. authorize payments based on the approved work plan and budget.
5. open and operate bank accounts in line with laws on be half of the office
6. delegate part of his powers and duties to the staff ,where necessary.
7. prepare and submit draft laws, directives concerning the office to the executive committee of the Amhara National Regional State for approval and implement the same up on approval
8. Submit periodic reports to the concerned body.
9. perform other functions as may be assigned to it by the executive committee and president of the region.

PART FOUR
Miscellaneous provisions

8. **Budget and Books of Accounts**
   1. The source of income of the office shall be the government and other sources
   2. The office shall have a complete and legal books of accounts
   3. Financial documents of the office shall be audited every year by the Auditor general and other auditors to be assigned by it .
9. **Transitory provisions**
   1. The office shall assist in auditing the accounts of cooperatives established prior to the issuance of this proclamation.
   2. On the basis of the findings of the audit

መድረሱን ካመነ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመነጋገር እንዲመለስ ጥረት ያደርጋል፤ ተገቢውን ሕጋዊ እርምጃ ለመውሰድ ሁኔታዎችን ያመቻቻል ።

3. በሽግግር መንግሥት በወጣው የገበሬዎች የኅብረት ሥራ አዋጅ ቁጥር 85/1986 ለግብርና ቢሮ ተሰጥቶ የነበረው የገበሬዎች ህብረት ስራ ማኅበራትን የመመዝገብና ህጋዊ ሰውነት የመስጠት ሥልጣን በዚህ አዋጅ ለጽ/ቤቱ ተላልፏል።

10. የመተባበር ግዴታ

ማንኛውም ጉዳዩ የሚመለከተው አካል ሁሉ የዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች በሥራ ላይ እንዲውሉ የመተባበር ግዴታ አለበት።

11. ተፈፃሚነት የሌላቸው ህጎች

ከዚህ አዋጅ ጋር የሚቃረን ማናቸውም ህግ በዚህ አዋጅ በተመለከቱት ጉዳዩች ላይ ተፈፃሚነት አይኖረውም።

12. መመሪያ የማውጣት ሥልጣን

ጽ/ቤቱ ይህን አዋጅ በሚገባ ሥራ ላይ ለማዋል የሚረዱ መመሪያዎችን ሊያወጣ ይችላል።

13. አዋጅ የማሻሻል ሥልጣን

ይህ አዋጅ ሊሻሻል የሚችለው በክልሉ ምክር ቤት ነው።

14. አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ በአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት ምክር ቤት ከፀደቀበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

ባሕር ዳር
መጋቢት 1 ቀን 1990 ዓ.ም
የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ምክር ቤት

discussing with concerned bodies, the office may make an effort to pay back the money embezzled or the property illegally taken.

3. All powers which were given to the bureau of agriculture pursuant to the agricultural cooperatives establishment proclamation No 85/1994 are here by transferred to the office.

10 Duty to cooperate

Any concerned organ shall have a duty to cooperate in the execution of provisions of this proclamation.

11. Inapplicable laws

Any law which is inconsistent with this proclamation shall not apply with respect to matters provided for here in.

12. **Power to issue directives**

The office may issue directives for the proper implementation of this proclamation.

13. **Power to amend the proclamation**

This proclamation can only be amended by the Regional council.

Effective Date

This proclamation shall come in to force from the date of its ratification by the council of the region

Done at Bahir Dar
This 10th day of march ,1998
The council of the Amhara National Regional State